www.fag.gov.et

የሰ/መ/ቁ 42901

ሐምሌ 21 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

በላቸው አንሺሶ

አመልካች፡- የትምህርት መሣሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት - ነገረ ፈጅ አቶ ጌታሁን ተስፋዬ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ንግሥት ለጥይበሉ - ጠበቃ አቶ አበራ ታደሰ ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሠጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

የክርክሩ ምክንያት የሥራ ክርክር ጉዳይ ሆኖ ተጠሪ ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ባቀረበችው ክስ ያለአግባብ የሥራ ውል የተቋረጠ በመሆኑ ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሎ ወደ ሥራ እንድመለስ አሊያም ተገቢ ክፍያዎች ተከፍሎ እንድሰናበት ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡

አመልካች ከሳሽ የሥራ መሪ እንጅ ሠራተኛ አይደለችም በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና የፍሬ ነገር ክርክር በማቅረብ መልስ በመስጠት ተከራክሯል፡፡

ግራ ቀኙን ያከራከረው የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሥራ ውል የተቋረጠው ከሕግ ወጪ ነው ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሎአት ወደ ሥራ ትመለስ ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት ከፍተኛ ፍ/ቤትም ውሳኔውን በማጽናቱ የቀረበ የሰበር አቤቱታ ነው፡፡

አመልካች ጥር 20 ቀን 2001 ዓ.ም ጽፎ ያቀረበውን ቅሬታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን የግራ ቀኙን የጽሑፍ ክርክር ሰምተናል፡፡ ጉዳዩ በሰበር ሰሚ ችሎት እንዲታይ የቀረበው ተጠሪ የሥራ መሪ ናቸው ወይንስ አይደሉም? የሚለውን ነጥብ ለመመርመር በመሆኑ ይህንኑ ከግራ ቀኙ ክርክርና ከሕጉ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

ከግራ ቀኙ ወገኖች ክርክር መረዳት የተቻለው ተጠሪ የድርጅቱ የሀገር ውስጥ ዕቃ ግዥ ዋና ክፍል ኃላፊ በመሆን እንዲሁም በተጨማሪነት የውጪ ሀገር ዕቃ ግዥ ዋና ክፍልና የሽያጭ ዋና ክፍልን የሚያካትተውን የንግድ መምሪያ ኃላፊነትን ደርበው ይሠሩ የነበረ መሆኑን ነው፡፡ ተጠሪ በእነዚህ መደቦች በኃላፊነት ስለመሥራታቸው አልተካደም፡፡ የሥራ መደቡ ዋና ተግባራት ምንድናቸው የሚለው ከተጠሪ የሥራ መዘርዝር /job description/ ሲታይ በአጠቃላይ በድርጅቱ መመሪያ መሠረት ማስተባበር፣ መምራት፣ ማደራጀት እና መቆጣጠር እንዲሁም ዕቅድና በጀት ዝግጅት ላይ መሳተፍ እንደሆነ የተመለከተ ሲሆን በድርጅቱ ጎብረት ስምምነት አንቀጽ 3 ንዑስ ቁጥር 3.3 እንደተመለከተው ስምምነቱ የዋና ክፍሎችንና የማምረቻ ኃላፊዎችን እንደማይጨምር በግልጽ ተመልክቷል፡፡ ተጠሪም ከሌሎች ሠራተኞች በተለየ ሁኔታ ከፍተኛ የድርጅቱ ኃላፊነት የተሠጠች መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ ከዚህ አንፃር ተጠሪ ሥራን የማቀድ፣ የመምራት፣ የመቆጣጠር፣ የማደራጀትና የማስተባበር ተግባራትን የሚያከናውኑ መሆኑን ከክርክሩም ሆነ ከቀረቡ ሰነዶች መረዳት ተችሏል፡፡ ስለዚህ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 3 በአዋጅ ቁጥር 494/98 አንቀጽ 2 እንደተሻሻለው ተጠሪ ከሥራ ተግባራቸው አንፃር የሥራ መሪ እንጅ ሠራተኛ አይደሉም፡፡ በአዋጁ ለሥራ መሪ የተሠጠው ትርጉም "የሥራ መሪ የሚባለው በሕግ ወይም እንደ ድርጅቱ የሥራ ፀባይ በአሠሪው በተሠጠው ውክልና ሥልጣን

መሠረት የሥራ አመራር ፖሊሲዎችን የማውጣትና የማስፈፀም ከዚህ በተጨማሪ ወይም እነዚህኑ ሳይጨምር ሠራተኛን መቅጠር ማዛወር የማገድ የማሰናበት የመመደበ ወይም የሥነ ሥርዓት እርምጃ የመውሰድ ተግባሮችን የሚያከናውንና የሚወስን ግለሰብ ነው ይላል፡፡" ከዚህ አንፃር የተጠሪ የሥራ ተግባር በፍሬ ነገር ረገድ የተረጋገጠው የድርጅቱን ዋና ክፍል ሥራ በኃላፊነት መምራት፣ ማደራጀት መቆጣጠርና ማስተባበር ከመሆኑ አንፃር በሕጉ ትርጉም ከተሠጠው የሥራ ዘርፍ የሚመደቡ በመሆናቸው የሥራ መሪ ናቸው እንጅ፤ ሠራተኛ አይደሉም፡፡ የመንግስት የልማት ድርጅቶች የቦርድም፣ የማናጅመንት አባላት ክፍያ አፈፃፀም መመሪያ እኔን አይጨምርም በማለት ከተጠሪ የቀረበውን ክርክር በተመለከተ መመሪያው ለቦርድና ማናጅመንት አባላት ሊከፈል የሚገባውን ክፍያ አስመልክቶ የወጣ የአፈፃፀም መመሪያ እንጅ ለተያዘው ጉዳይ ተፈፃሚ ስለማይሆን ክርክሩ አግባብነት የሌለው ነው፡፡ በአጠቃላይ ከላይ በተጠቀሱ ምክንያቶች እና በሰበር መ/ቁጥር 40055 በተመሳሳይ ጉዳይ ትርጉም የተሠጠበት በመሆኑ ተጠሪ የሥራ መሪ እንጅ ሠራተኛ ባለመሆናቸው ጉዳያቸው በሥራ ክርክር ችሎት ክስ ለማቅረብም ሆነ ክርክር ለማካሄድና ዳኝነት ለማግኘት የሚችሉበት የሕግ አግባብ ስለሌለ የመጀመሪያ ደረጃ እና ከፍተኛ ፍ/ቤቶች የሠጡት ውሳኔ በሕግ ረገድ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ውሳኔ ነው ብለናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 13197 በ18/12/2000 ዓ.ም እንዲሁም ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 73934 በ18/5/2000 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሠጡት ውሳኔዎች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁ 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. ተጠሪ የሥራ መሪ በመሆናቸው ጉዳያቸው በሌላ ሕግ ከሚታይ በቀር በሥራ ክርክር ችሎት ሊታይ አይችልም ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ